መንዝ ውስጥ የሚገኙ ቅዱሳን ቦታ እመጓ ኡራኤል

ይህ ቦታ ከሞላሌ ከተማ በስተ ምእራብ አቅጣጫ የ 2 ሰአት ከ 30 ደቂቃ የእግር ጉዞ ከተጓዙ በኋላ የሚገኝ ሲሆን ቤተ ክርስትያኑን ያሰሩት አጼ ናኦድ እንደሆኑ በድርሳኑ ላይ ተጽፎ ይገኛል። በዚህ ቦታ በአመት አንድ ጊዜ የእርገት በአል በድምቀት ተከብሮ ይውላል። ቦታው ቅዱስ ዑራኤል የጌታችንን ቅዱስ ደም የረጨበት ሲሆን በአሁኑ ሰአት በየአመቱ የእርገት በአል ሲከበር መላኩ ቅዱስ ኡራኤል የጌታን ደም የረጨበት ቦታ ድረስ ምእመናን ከተለያዩ አካባቢዎች በመምጣት እየጎበኙ በረከትን እያገኙ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ አካባቢ የቅዱስ ጊዮርጊስ ፈረሶች ከተራራ ተራራ እየዘለሉ ለብዙ ዘመናት የአካባቢውን ማህበረሰብ ያሰቃይ የነበረውን ሰይጣን ድል ለመንሳት ሲዋጉ ፈረሶቹ የረገጡት የእግራቸው ኮቴ ቅርጽ ድንጋይ ላይ ቀርቶ የሚታይበት ተአምረኛ ቦታ ነው። በተጨማሪም ከዚህ ቦታ በስተ ደቡብ ምእራብ በኩል በገደሉ ስር በአፄ ናኦድ ዘመነ መንግስት የተመሰረተች ቀጭን አምባ ማርያም የምትባል ቤተክርስትያን ስትገኝ በዚች ቅድስት ቦታ ብዙ ተአምራት የተደረጉ ሲሆን ከነዚህም መካከል በጌታችን የስቅለት እለት አጋንንት ወደ ሲኦል የወረዱበት አስደናቂ ቦታ ይገኛል።





ይህ ገዳም መንዝ ውስጥ የሚገኝ /እመጋል ቆጵሮስ ኢየሱስ ቅዱስ ኡራኤል /ገዳም

ይህ ቦታ--

፩-ድንግል ማርያም ከልጅዋ ጋር በተሰደደች ግዜ የተቀመጠችበት ቦታ ነው።

፪-የቦታውን ስም እራሱ ጌታቸን ነው ስሙን ያወጣው /እመጋል/ብሎ።እመጋል ሲለው /የእኔና የአንች ሀገር (የእናትና የልጅ)ሀገር ብሎታል

፫-በቦታው 2 ተራራ አለ:---- 1-ገሊላ (ክሊና) ተራራ:-ይህ ተራራ እመቤታችን የተቀመጠችበት ና ጌታችን ኢትዮጵያን አስራት ሀገርሽ ትሁንሽ ብሎ ያረገበት ቦታ ነው።በተራራው ላይ በአየር ላይ የቆመ ድንጋይ ይታያል ፡በድንጋው ላይ ተወጥቶ 3 ግዜ ይዞራል

2-ቆጵሮስ ተራራ:-ይህ ተራራ ቅዱስ ኡራኤል የጌታን ደም የረጨበት ጽዋ (መነሳነስ) የሰወረበት ተራራ ነው የሰወረበት ቦታ ይታያል።

፬-በዚህ ቦታ ጌታችን ለቅዱስ ጊዮርጊስ ኢትዮጵያን አስራት ሀገርህ ነች ብሎት ያረገበት ቦታና የቅዱስ ጊዮርጊስ የፈረሱ የ 4 ቱ የእግሩ አሻራ በድንጋይ ላይ ታትሞ ይታያል።

፭-በቦታው ላይ ዋሻ አለ ::በዋሻው ውስጥ:- -/ የድንግል ማርያም የእጅዋ አሻራ በድንጋይ ታትሞ ይታያል

-ያልፈረሰ;ያልበሰበሰ ክንፍ ያላቸው አፅመ ቅድሳን አጽም ይታያል

-የድንግልና የልጅዋ ልብስ እንዳለ ይነገራል

-የሚጠበቀው ዋሻው በነጭ ነብርና በነጭ አንበሳ ነው ይታያሉ

፮-በዚሁ አካባቢ የማርያም ገዳም አለ የማርያም ቤተክርስቲያን ያረፈበት ቦታ ድንግል የተቀመጠችበትን ቦታ ቅዱስ ኡራኤል በክፉ የጠረገው ቦታ ነው ቤተክርስቲያን የተሰራው።

የቦታው ቃልኪዳን:-ቦታው የረገጠ (የቦታውን አካባቢ አሻግሮ ያየ)189 ትውልድ ያለ ንስሀ እምረዋለሁ የጠየቀውን የህሳቡን እሰጠዋለሁ;እምረዋለሁ።



በረከቱ ይደርባችሁ አሜን አሜን አሜን!!!

እመጓ መንዝ ኡራኤል:- ምድር ደበሎ ማዕዛ ቅዱሳን ሚዲያ